401/2013

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን
Federal Democratic Republic of Ethiopia
CIVIL SERVICE COMMISSION

ቁጥር/Ref.No. ሲሠኮ/ህዐ/204/2012

ቀን/ Date 17 የካቲት 2012

**በዝርዝሩ ለተመለከቱት**
**<u>አዲስ አበባ</u>**

ጉዳዩ፡- <u>የቀን የውሎ አበል ማሻሻያ አፈጻጸም መመሪያን ስለመላክ</u>

የመንግሥት ሠራተኞች ከመደበኛ የሥራ ቦታ ክልል ውጭ ወደሆኑ የሥራ ቦታዎች ለሥራ ጉዳይ ሲንቀሳቀሱ የምግብና የመኝታ ወጪ ለመሸፈን የቀን የውሎ አበል መመሪያ በማውጣት በሥራ ላይ እንዲውል ከመስሪያ ቤታችን ሰኔ 29/2004 ዓ.ም በቁጥር ሲ.ሰ.ሚ30/ጠ13/40/883 በተጻፈ ደብዳቤ መሠረት መተላለፉ ይታወሳል፡፡

በመሆኑም በመመሪያው ተፈቅዶ የነበረው የአበል መጠን ከወቅቱ የገበያ ዋጋ ጋር ባለመመጣጠኑ፣ ለአከፋፈል ምቹ ባለመሆኑ እና በመስክ የሥራ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ በማሳደሩ የመንግሥትን የመክፈል አቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት መጠነኛ ማሻሻያ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የካቲት 7 ቀን 2012 ዓ.ም. ባካሄደው 5ኛ የምርጫ ዘመን 79ኛ መደበኛ ስብሰባ የመንግሥት ሠራተኞችን የቀን የውሎ አበል ተመንና የአከፋፈል ሥርዓትን መርምሮ ከየካቲት 16 ቀን 2012 ዓ.ም. ጀምሮ በሥራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

ስለሆነም በምክር ቤቱ የጸደቀውን የቀን የውሎ አበል መመሪያ ከዚህ ሸኚ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እየገለጽን፣ መመሪያው በየተቋሙ በትክክል ተፈጻሚ መደረጉን የገንዘብ ሚኒስቴር፣ የፋይናንስ ቢሮዎች፣ የተቋም የበላይ ኃላፊዎች፣ የኦዲት ባለሙያዎች እና ሌሎች የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ሁሉ ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር እንዲያደርጉ እናሳስባለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

በዛብህ ገብረየስ በየነ
ኮሚሽነር

<u>ግልባጭ</u>

- ለኮሚሽነር ጽ/ቤት
- ለም/ ኮሚሽነር ጽ/ቤት
- ለሰው ሀብት ኦዲት ዳይሬክቶሬት
- ለአደረጃጀት፣ የስራ ምዘናና ክፍያ ጥናት ዳይሬክቶሬት

<u>ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን</u>

ስልክ/Tel: +251 115 54 96 66/67
ፋክስ/Fax: +251 115549707
ፖ.ሳ.ቁ. 1082
Email: contactus@ecsc.gov.et
Website:- www.ecsc.gov.et
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

ማገልገል ክብር ነው! ድህነትን ለማሸነፍ ማገልገል ደግሞ ድርብ ክብር ነው!
Serving to Beat Poverty is Double Honor!

| ተ.ቁ | የመሥሪያ ቤቶች ስም ዝርዝር | አድራሻ |
|---|---|---|
| | **ሚኒስቴር** | |
| 1. | ለሰላም ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 2. | ለሀገር መከላከያ ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 3. | ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 4. | ለገንዘብ ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 5. | ለግብርና ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 6. | ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 7. | ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 8. | ለትራንስፖርት ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 9. | ለከተማ ልማት ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 10. | ለውሃ፣መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 11. | ለማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 12. | ለትምህርት ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 13. | ለሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 14. | ለጤና ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 15. | ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 16. | ለገቢዎች ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 17. | ለሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 18. | ለሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 19. | ለጠቅላይ ዓቃቤ ህግ | አዲስ አበባ |
| | **ኮሚሽን** | |
| 20. | ለሰብአዊ መብት ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 21. | ለፌዴራል የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 22. | ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 23. | ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 24. | ለአካባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 25. | ለሥራ ዕድል ፈጠራ ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 26. | ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 27. | ለግምሩክ ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 28. | ለብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 29. | ለመስኖ ልማት ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 30. | ለውሃ ልማት ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 31. | ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 32. | ለስፖርት ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 33. | ለኘላንና ልማት ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 34. | ለዕርቀ ሰላም ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 35. | የአስተዳደር ጉዳዮች፣ የወሰንና ማንነት ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| | **ባለስልጣን** | |
| 36. | ለብሮድካስት ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 37. | ለቡናና ሻይ ልማትና ግብይት ባለሥልጣን | አዲስ አበባ |

| | | |
|---|---|---|
| 38. | ለእንስሳት መድሃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 39. | ለፌዴራል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪግ ኢንዱስትሪዎች ማስፋፊያ ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 40. | ለንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 41. | ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 42. | ለኢትዮጵያ ጨረራ መከላከል ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 43. | ለኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 44. | ለፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 45. | ለማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 46. | ለኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን | አዲስ አበባ |
| 47. | ለኮንስትራክሽን ሥራዎች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 48. | ለተፋሰሶች ልማት ባለሥልጣን | አዲስ አበባ |
| 49. | ለኢትዮጵያ ኢነርጅ ባለሥልጣን | አዲስ አበባ |
| 50. | ለኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለሥልጣን | አዲስ አበባ |
| 51. | ለቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን | አዲስ አበባ |
| 52. | ለኢትዮጵያ ዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን | አዲስ አበባ |
| | **ኤጀንሲ** | |
| 53. | ለፌዴራል ከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 54. | ለኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 55. | ለመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 56. | ለኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 57. | ለኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነቶች ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 58. | ለዲያስፖራ ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 59. | ለመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 60. | ለመንግሥት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 61. | የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 62. | ለሠነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 63. | ለህብረት ሥራ ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 64. | ለግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 65. | ለኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 66. | ለመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 67. | ለፌዴራል ከተሞች የሥራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 68. | ለፌዴራል ለተቀናጀ መሠረተ ልማት ማስተባበሪያ ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 69. | ለብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 70. | ለሀገር አቀፍ ትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 71. | ለከፍተኛ ትምህርት አግባቡነትና ጥራት ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 72. | ለመድሃኒት አቅራቢ ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 73. | ለኢትዮጵያ ጤና መድህን ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 74. | ለግል ድርጅት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 75. | ለስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ | |

| | | |
|---|---|---|
| 76. | ለብሔራዊ ቤተ-መዛግብትና ቤተ-መጻህፍት ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 77. | ለማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 78. | ለፌዴራል ቴክኒክና ትምህርት ሙያ ስልጠና ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| | **ጽ/ቤት** | |
| 79. | ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 80. | ለፕሬዚዳንት ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 81. | ለህገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 82. | ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 83. | ለኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 84. | ለመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 85. | ለታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪ ኘሮጀክት ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 86. | ለብሔራዊ የኤች አይ.ቪ./ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 87. | ፀረ-አበረታች ቅመሞች ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| | **ምክር ቤት** | |
| 88. | ለፌዴሬሽን ምክር ቤት | አዲስ አበባ |
| 89. | ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት | አዲስ አበባ |
| | **ፍርድ ቤት** | |
| 90. | ለጠቅላይ ፍርድ ቤት | አዲስ አበባ |
| 91. | ለከፍተኛ ፍርድ ቤት | አዲስ አበባ |
| 92. | ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት | አዲስ አበባ |
| 93. | ለጠቅላይ ሸሪያ ፍርድ ቤት | አዲስ አበባ |
| | **ኢንስቲትዩት** | |
| 94. | ለኢትዮጵያ ከይዘን ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 95. | ለኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ስትራቴጂክ ጥናት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 96. | ለውጭ ግንኙነት አገልግሎት ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 97. | ለፍትህና የሕግ ምርምርና ስልጠና ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 98. | ለኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 99. | ለብሔራዊ እንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 100. | ለብሔራዊ የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 101. | ለጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 102. | ለቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 103. | ለብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 104. | ለምግብ፣የመጠጥና የፋርማሲቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 105. | ለኬሚካልና የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 106. | ለስጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | ደብረዘይት |
| 107. | ለኢትዮጵያ ብሔራዊ የስነ-ልክ ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 108. | ለኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 109. | ለኢትዮጵያ ባዮቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |

| | | |
|---|---|---|
| 110. | ለቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 111. | ለጂኦስፓሻል ኢንፎርሜሽን ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 112. | ለኮንስትራክሽን ሥራዎች ኘሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 113. | ለውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቱትዩት | አዲስ አበባ |
| 114. | ለፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትስልጠና ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 115. | ለኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 116. | የአርማወር ሐንሰን የምርምር ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 117. | ለፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 118. | ለኢትዮጵያ ብዝሃ-ህይወት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 119. | ለኢትዮጵያ አካባቢና ደን ምርምር ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| | **ማዕከል** | |
| 120. | ለፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል | አዲስ አበባ |
| 121. | ለብሔራዊ የእንስሳት ጤና ምርምርና ጥናት ማዕከል | ሰበታ |
| 122. | ለኢትዮጵያ የገጠር ኢነርጂ ልማት ማስፋፊያ ማዕከል | አዲስ አበባ |
| 123. | ለከፍተኛ ትምህርት ስትራቴጂክ ማዕከል | አዲስ አበባ |
| 124. | ለመላ አፍሪካ ስጋ ደዌ መካላከያና ትምህርት መስጫ ማዕከል | አዲስ አበባ |
| 125. | ለሆቴሎችና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል | አዲስ አበባ |
| 126. | ለአትሌት ጥሩነሽ ዲባባ አትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከል | አዲስ አበባ |
| 127. | ለገፈርሳ የአዕምሮ ህሙማን ማገገሚያ ማዕከል | |
| | **አስተዳደር** | |
| 128. | ለፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር | አዲስ አበባ |
| 129. | ለቤተ መንግሥት አስተዳደር | አዲስ አበባ |
| 130. | ለብሔራዊ ሎቶሪ አስተዳደር | አዲስ አበባ |
| | **ኮሌጅ** | |
| 131. | ለሚዛን የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ | ሚዛን |
| 132. | ለአጋርፋ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ | አጋርፋ |
| 133. | ለቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታልና ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ | አዲስ አበባ |
| 134. | ለአላጌ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ | አላጌ |
| 135. | ለአርዳይታ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ | አርዳይታ |
| 136. | ለገዋኔ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ | ገዋኔ |
| | **ዩኒቨርስቲ** | |
| 137. | ለሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ | አዲስ አበባ |
| 138. | ለአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ | አዲስ አበባ |
| 139. | ለአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ | አዳማ |
| 140. | ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ | አዲስ አበባ |
| 141. | ለወለጋ ዩኒቨርሲቲ | ነቀምቴ |
| 142. | ለድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ | ድሬዳዋ |
| 143. | ለደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ | ደብረብርሃን |
| 144. | ለመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ | ባሌ |
| 145. | ለመቐሌ ዩኒቨርሲቲ | መቐሌ |
| 146. | ለሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ | ሚዛን |

| | | |
|---|---|---|
| 147. | ለጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ | ጅግጅጋ |
| 148. | ለአክሱም ዩኒቨርስቲ | አክሱም |
| 149. | ለሰመራ ዩኒቨርስቲ | ሰመራ |
| 150. | ለደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ | ደብረማርቆስ |
| 151. | ለአምቦ ዩኒቨርሲቲ | አምቦ |
| 152. | ለጅማ ዩኒቨርሲቲ | ጅማ |
| 153. | ለአርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ | አርባ ምንጭ |
| 154. | ለሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ | ሀሮማያ |
| 155. | ለዲላ ዩኒቨርሲቲ | ዲላ |
| 156. | ለጎንደር ዩኒቨርሲቲ | ጎንደር |
| 157. | ለሃዋሣ ዩኒቨርሲቲ | ሃዋሳ |
| 158. | ለወሎ ዩኒቨርሲቲ | ወሎ |
| 159. | ለመቱ ዩኒቨርሲቲ | መቱ |
| 160. | ለአዲግራት ዩኒቨርሲቲ | አዲግራት |
| 161. | ለቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ | ቡሌ ሆራ |
| 162. | ለወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ | ወልቂጤ |
| 163. | ለአሶሳ ዩኒቨርሲቲ | አሶሳ |
| 164. | ለወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ | ሶዶ |
| 165. | ለወልዲያ ዩኒቨርሲቲ | ወልዲያ |
| 166. | ለባህርዳር ዩኒቨርሲቲ | ባህር ዳር |
| 167. | ለደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ | ደብረ ታቦር |
| 168. | ለጋምቤላ ዩኒቨርስቲ | ጋምቤላ |
| 169. | ለአርሲ ዩኒቨርስቲ | አርሲ |
| 170. | ለዋቻሞ ዩኒቨርሲቲ | ሆሳዕና |
| 171. | ለወራቤ ዩኒቨርስቲ | ወራቤ |
| 172. | ለቦንጋ ዩኒቨርስቲ | ቦንጋ |
| 173. | ለመቅደላ ዩኒቨርስቲ | መቅደላ |
| 174. | ለደባርቅ ዩኒቨርስቲ | ደባርቅ |
| 175. | ለደንቢዶሎ ዩኒቨርስቲ | ደንቢዶሎ |
| 176. | ለእንጅባራ ዩኒቨርስቲ | እንጅብራ |
| 177. | ለኦዳቡልቱም ዩኒቨርስቲ | ጭሮ |
| 178. | ለሰላሌ ዩኒቨርስቲ | ሰላሌ |
| 179. | ለራያ ዩኒቨርስቲ | ራያ |
| 180. | ለጂንካ ዩኒቨርስቲ | ጂንካ |
| 181. | ለቀብሪደሀር ዩኒቨርስቲ | ቀብሪደሃር |
| | **አካዳሚ** | |
| 182. | ለመለስ ዜናዊ አመራር አካዳሚ | አዲስ አበባ |
| 183. | ለኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ | አዲስ አበባ |
| | **ቦርድ** | |
| 184. | ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ | አዲስ አበባ |
| 185. | ለኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ | አዲስ አበባ |

| | | |
|---|---|---|
| | **አገልግሎት** | |
| 186. | ለብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት | አዲስ አበባ |
| 187. | ለመንግሥት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት | አዲስ አበባ |
| 188. | ለብሄራዊ የደም ባንክ አገልግሎት | አዲስ አበባ |
| | **ሆስፒታል** | |
| 189. | ለቅዱስ ጴጥሮስ ቲቪ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል | አዲስ አበባ |
| 190. | ለቅዱስ አማኑኤል አዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል | አዲስ አበባ |
| 191. | አቤት ሆስፒታል | አዲስ አበባ |
| | **ልዩ ልዩ** | |
| 192. | ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር | አዲስ አበባ |
| 193. | ለህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም | አዲስ አበባ |
| 194. | ለውሃ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 195. | ለዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት | አዲስ አበባ |
| 196. | ለቱሪዝም ኢትዮጵያ | አዲስ አበባ |
| 197. | ለኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ | አዲስ አበባ |
| 198. | ለግብርና ምርምር ካውንስል ሴክሬታሪያት | አዲስ አበባ |
| 199. | ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት | አዲስ አበባ |
| | **ክልል/የከተማ መስተዳድር** | |
| 1. | ለኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ፐብሊክ ሰርቪስና መልካም አስተዳደር ቢሮ | አዲስ አበባ |
| 2. | ለአማራ ብ/ክ/መንግስት ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ | ባህርዳር |
| 3. | ለደቡብ ብ/ብ/ህ/ብ/ክ/መንግስት ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | ሀዋሳ |
| 4. | ለትግራይ ብ/ክ/መንግስት ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | መቐሌ |
| 5. | ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | አዲስ አበባ |
| 6. | ለድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | ድሬዳዋ |
| 7. | ለሐረሪ ብ/ክ/መንግስት ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | ሐረሪ |
| 8. | ለሶማሌ ብ/ክ/መንግስት ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | ጅግጅጋ |
| 9. | ለአፋር ብ/ክ/መንግስት ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | ሰመራ |
| 10. | ለጋምቤላ ብ/ክ/መንግስት ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | ጋምቤላ |
| 11. | ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/መንግስት ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ | አሶሳ |

# የመንግሥት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር

# 401/2013

የካቲት/2012 ዓ.ም

<u>አዲስ አበባ</u>

# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

## የመንግሥት ሠራተኞች የአገር ውስጥ የቀን ውሎ አበል ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ **401/2013**

የመንግሥት ሠራተኞች ከመደበኛ ሥራ ቦታ ክልል ውጭ ለሥራ ሲንቀሳቀሱ ለምግብና ለመኝታ የሚያወጡትን ወጪ በቀን ውሎ አበል መሸፈን ያለበት በመሆኑ፣ ከዚህ በፊት ሲሠራበት የነበረው የቀን ውሎ አበል ተመን ከወቅታዊ የገበያ ሁኔታዎች ጋር ተጣጥሞ ስላልተሻሻለ በየጊዜው እያደገ የሚሄደውን የምግብና የመኝታ ዋጋ ጋር ባለመሸፈኑ በሠራተኞችና በመንግሥት ሥራ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ በማሳደሩ፣ ለአከፋፈልም ምቹ ባለመሆኑ የአሰራር ማሻሻያ ማድረግ በማስፈለጉ፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የካቲት 07 ቀን 2012 ዓ.ም. ባካሄደው 5ኛ የምርጫ ዘመን 79ኛ መደበኛ ስብሰባ በመንግሥት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል ተመንና አከፋፈል ሥርዓት ላይ ተወያይቶ ባሳለፈው ውሳኔ መሠረት የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሠ) እና በመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### አንቀጽ 1

### አውጪው ባለሥልጣን

የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የፌዴራል አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሠ) እና በመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## አንቀጽ 2

## አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የመንግሥት ሠራተኞች የአገር ውስጥ የቀን ውሎ አበል ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 3/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 3

## ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "የመንግሥት ሠራተኛ" ማለት በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ተቀጥሮ በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ የሚያገለግል ማንኛውም ሠራተኛና የሥራ ኃላፊ ነው፡፡
2. "የቀን ውሎ አበል" ማለት አንድ የመንግሥት ሠራተኛ በአገር ውስጥ ከመደበኛ የሥራ ቦታ ውጭ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ ለሥራ ጉዳይ ሄዶ በዕለቱ ለመመለስ ሳይችል ሲቀር ለአንድ ቀን ለሚያስፈልገው የምግብና የመኝታ ወጪ የሚከፈል አበል ነው፡፡
3. "የውሎ ገባ አበል" ማለት አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ከመደበኛ የሥራ ቦታ ውጪ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ ሄዶ ዕለቱን የሚመለስ ከሆነ ለምግብ ለሚያወጣው ወጪ የሚከፈል አበል ነው፡፡
4. "የአየር ፀባይ አበል" ማለት አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ለመስክ ሥራ የአየር ጸባዩ አስቸጋሪ ወደ ሆነ ቦታ ሲንቀሳቀስ የሚከፈል አበል ነው፡፡
5. በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

## አንቀጽ 4

## የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን

ከመንግሥት ተሿሚዎች በስተቀር ከፌዴራል እስከ ቀበሌ አስተዳደር እርከን ድረስ በአገር አቀፍ ደረጃ በዜግነት ኢትዮጵያዊ በሆኑ በቋሚ እና ጊዜያዊነት ወይም በኮንትራት ተቀጥረው በሚያገለግሉ የመንግሥት ሠራተኞች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የቀን ውሎ አበል ክፍያ አፈጻጸም

### አንቀጽ 5

### የቀን ውሎ አበል ተመንና አከፋፈል

1. የቀን ውሎ አበል ተመን የሚሰላው ከአንድ ቀን የውሎ አበል ክፍያ ውስጥ ለቁርስ 10%፣ ለምሳ 25 %፣ ለእራት 25% እና ለአልጋ 40% በመመደብ ነው፡፡
2. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ከመደበኛ የሥራ ቦታው ውጪ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ ለሥራ ጉዳይ ሄዶ ዕለቱን መመለስ ካልቻለ ለሥራ ተሰማርቶ ቁርስ፣ ምሳ እና እራት በተመገበባቸው የክልል፣ የዞንና የወረዳ ከተማ ወይም የከተማ አስተዳደሮች እንዲከፈል የተመደበውን የውሎ አበል ክፍያ ለእያንዳንዱ ቀን በዚህ መመሪያ ከሠንጠረዥ አንድ እስከ አራት በተመለከተው መሠረት፣
   - ሀ) የክልል ዋና ከተማ የተመደበው በሠንጠረዥ 1 የተመለከተው፣
   - ለ) ለአዳማ ከተማ አስተዳደር ለከተማ አስተዳደሩ የተመደበው ሠንጠረዥ 2 የተመለከተው፣
   - ሐ) ለዞን ዋና ከተማ በየክልሉ ለዞን ዋና ከተሞች የተመደበው በሠንጠረዥ 3 የተመለከተው፣
   - መ) በወረዳ ከተማ ወይም የከተማ አስተዳደሮች በየክልሉ በወረዳ ከተማ ወይም የከተማ አስተዳደሮች ዋና ከተሞች በሠንጠረዥ 4 የተመለከተው፣

   በደመወዝ መጠናቸው መሠረት ይከፈላል፡፡
3. አንዳንድ የክልልና የዞን ከተሞች ሆነው የወረዳ ከተማ መቀመጫዎች በሆኑበት ለክልሎች ወይም ለዞን ከተማዎች የተመደበው የቀን ውሎ አበል ተመን ለወረዳው ከተማ ጭምር የሚያገለግል ይሆናል፡፡
4. የገጠር ቀበሌ የቀን ውሎ አበል በደመወዝ ደረጃ ልዩነት ሳይደረግ ለሁሉም የመንግሥት ሠራተኛ ቀደም ሲል ተወስኖ በሥራ ላይ ያለው ብር 100 የሚቀጥል ይሆናል፡፡

5. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በመስራት ላይ ያለ የመንግሥት ሠራተኛ ቀድሞ በተያዘ እቅድ መሠረት በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ውስጥ ለሥራ ተንቀሳቅሶ ለምሳ ወደ መደበኛ የሥራ ቦታው መመለስ የማይችል ከሆነ እቅዱ ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ቀርቦ ሲጸድቅ ብቻ ለአዲስ አበባ ከተማ ከተፈቀደው የቀን ውሎ አበል በደመወዝ መጠኑ መሠረት 25% ለምሳ ይከፈለዋል፡፡
6. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ከመደበኛ የሥራ ቦታው ውጪ ወደ ሆነ ሌላ የሥራ ቦታ ለሥራ ጉዳይ ሄዶ መሥሪያ ቤቱ የምግብ ወይም የመኝታ አገልግሎት የሰጠ እንደሆነ የተሰጠው የአገልግሎት ሂሳብ ከሚከፈለው የቀን ውሎ አበል ላይ ተቀናሽ ይሆናል፡፡
7. ይህ መመሪያ በሥራ ላይ ከዋለ በኋላ አዲስ የሚደራጁ የዞን ወይም ወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ሲኖሩ የቀን ውሉ አበል መጠኑ ቀድሞ ተደራጅቶበት ለነበረው የዞን ወይም ወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የተመደበው የቀን ውሎ አበል መጠን ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 6

## የውሎ ገባ አበል አከፋፈል

1. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ለሥራ ጉዳይ ከመደበኛ የሥራ ቦታ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ ሄዶ ከጠዋቱ አንድ ሰዓት በፊት የሚንቀሳቀስ ከሆነ ለቁርስ፣ በዕለቱ ከ 6:30 በኋላ የሚመለስ ከሆነ የምሳ እና ከምሽቱ 2:00 ሰዓት በኋላ የሚመለስ ከሆነ ለእራት ሥራውን ሲያከናውን በዋለበት ለክልል ከተማ፣ ለዞን ከተማ ወይም ለወረዳ ከተማ እንዲከፈል የተመደበው የቀን ውሎ አበል ሂሳብ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ይከፈለዋል፡፡
2. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 5 ከተመለከተው በስተቀር መደበኛ የሥራ ቦታ በሚገኝበት የክልል ወይም የዞን ወይም የወረዳ ከተማ ውስጥ በመዘዋወር ሥራውን ለሚያከናውን የመንግሥት ሠራተኛ የውሎ ገባ አበል አይከፈልም፡፡

## አንቀጽ 7

## የአየር ጠባይ አበል ወደሚከፈልበት የሥራ ቦታ ለሚላክ ሠራተኛ የሚከፈል የቀን ውሎ አበል

አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ለሥራ ጉዳይ የአየር ጸባይ አበል ወደሚከፈልበት የሥራ ቦታ ሲላክ፡-

1. በአንደኛ ደረጃ 40% የአየር ጸባይ አበል ወደሚከፈልበት የሥራ ቦታ የተመደበ ከሆነ የቀን ውሎ አበሉ 40% በተጨማሪነት ተሰልቶ ይከፈለዋል፡፡
2. በሁለተኛ ደረጃ 30% የአየር ጸባይ አበል ወደሚከፈልበት የሥራ ቦታ የተመደበ ከሆነ የቀን ውሎ አበሉ 30% በተጨማሪነት ተሰልቶ ይከፈለዋል፡፡
3. በሶስተኛ ደረጃ 20% የአየር ጸባይ አበል ወደሚከፈልበት የሥራ ቦታ የተመደበ ከሆነ የውሎ አበሉ 20% በተጨማሪነት ተሰልቶ ይከፈለዋል፡፡

## አንቀጽ 8

## የቀን ውሎ አበል የሚከፈልበት የጊዜ ወሰን

1. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ከመደበኛ የሥራ ቦታ ውጭ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ ተልኮ ያለማቋረጥ በመሥራት በአንድ ቦታ እስከ አንድ ወር የቆየ እንደሆነ ለቆየባቸው ቀናት የቀን ውሎ አበል ይከፈለዋል፡፡ ሆኖም ሥራው ከአንድ ወር ለበለጠ ጊዜ የሚቆይ መሆኑ ሲረጋገጥ የመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ በተጨማሪ እስከ ሁለት ወር የአበል ክፍያ እንዲቀጥል ሊፈቅድ ይችላል፡፡
2. አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ሥራው በፕሮግራም የተደገፈ ሆኖ ከመደበኛ የሥራ ቦታ ውጭ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ ተልኮ የሚቆይበት ጊዜ ከሶስት ወር በላይ የሚፈጅ መሆኑ በቅድሚያ ከተረጋገጠ እና በመስሪያ ቤቱ የበላይ ሀላፊ ሲፈቀድ ሠራተኛው የሥራ መደቡ ወደሚገኝበት ቦታ በመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 28(2) እና አንቀጽ 29 (1 - 4) መሠረት እንዳስፈላጊነቱ እንዲዘዋወር ማድረግ ይቻላል፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ቢኖርም በሥራ ባህሪያቸው አስገዳጅነት ከፌዴራልና ከክልል ከመደበኛ የሥራ ቦታቸው በመራቅ ከሶስት ወር በላይ ለሚቆዩ የመንግሥት ሠራተኞች ሥራውን በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ባለሙያ መድቦ ማሰራት የማይችል መሆኑ ከታመነበት እና በጀት አስቀድሞ መያዙ ሲረጋገጥ የተቋሙ የበላይ ኃላፊ ሥራው እስኪጠናቀቅ የመስክ ቆይታ ጊዜውን ሊፈቅድ ይችላል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 9

### ለቀን ውሎ አበል ክፍያ የሚሞሉ ቅጾች

1. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ከመደበኛ የሥራ ቦታ ውጭ ወደ ሌላ ሥራ ቦታ ለሥራ ጉዳይ ከመላኩ በፊት የቀን ውሎ አበል መጠየቂያ፣ መክፈያና መፍቀጃ ቅጾች ለጉዳዩ አግባብ ባላው ሠራተኛ ወይም የሥራ ኃላፊ እንዲሞሉ ይደረጋል፡፡
2. የቀን ውሎ አበል እንዲከፈል የጠየቀ የሥራ ኃላፊ በሠራተኛ የተሞላ ቅጽ በትክክል መሞላቱን ያረጋግጣል፡፡
3. የቀን ውሎ አበል እየተከፈለው ወደ ሌላ የሥራ ቦታ የተላከ የመንግሥት ሠራተኛ ሥራውን አጠናቆ ሲመለስ የቀን ውሎ አበል መቆጣጠሪያና የሥራ ክንውን መመዝገቢያ ቅጽ በመሙላት ስላከናወናቸው ሥራዎች መግለጫ እንዲያቀርብ ይደረጋል፡፡
4. የቀን ውሎ አበል ክፍያ እንዲፀድቅለት የሚጠይቅ የስራ ኃላፊ የመስክ ጉዞ ሪፖርት መቀበሉን የሚያረጋግጥ መግለጫ በማፅደቂያ ሰነዶች ላይ ማመላከት አለበት፡፡
5. በአባሪነት የተካተቱት ሠንጠረዦች እና ቅጾች የመመሪያው አካል ናቸው፡፡

### አንቀጽ 10

### የመንግሥት ሀብትን በቁጠባ ስለመጠቀምና የመቆጣጠሪያ ዘዴዎች

1. በፌደራል ተቋማት፣ በሁሉም ክልሎችና ሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች በጀት በሚያዝበት ወቅት በአመቱ የመስክ ሥራ የሚመለከታቸው ሠራተኞች ተለይተው ለምን ያህል ቀናት እንደሚሰማሩ እቅድ መያዝ እና የተያዘውም በጀት ከፕሮግራም በጀት አሠራር ጋር እንዲተሳሰር ማድረግ ይገባል።

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በበጀት ዝግጅት ወቅት በመሥሪያ ቤቱ እቅድ ያልተካተተ ስራ ሆኖ ይህንኑ አለማከናወን በመሥሪያ ቤቱ የተልዕኮ አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊፈጥር የሚችል ሲሆን፣ ችግሩን ሊያቃልል የሚችል እቅድ ቀርቦ በተቋሙ የበላይ ሀላፊ ሲፈቀድ ብቻ የመስክ ጉዞው እንዲካሄድ ማድረግ ይቻላል፡፡

3. የመንግሥት ሠራተኞች ለመስክ ሥራ እንዲሰማሩ ሲደረግ ለሥራ ከሚቆዩበት ቀናት ውጪ የተጨማሪ ቀናት ትርፍ ክፍያ እንዳይፈጸም በፌዴራል ገንዘብ ሚኒስቴርና በክልሎችና ሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች የገንዘብ ቢሮዎች አማካይነት በካሽ ፍሎው ማኔጅመንት ሂደት ላይ ተገቢው ክትትል ይደረጋል።

4. በየበጀት ዓመቱ በመንግሥት የውሎ አበል በጀት የሚሸፈን የመስክ ጉዞ ስምሪት ከ90 ቀናት እንዳይበልጥ ቁጥጥር ይደረጋል።

5. የውሎ አበል ክፍያ በፌዴራልም ሆነ በክልሎች የኦዲት መ/ቤቶች የስጋት ክትትልና ቁጥጥር ቅድሚያ መስፈርት ሆኖ እየተሰራበት መሆኑ እንዳለ ሆኖ ወደፊትም «የውሎ አበል ክፍያና የመስክ ጉዞ» ጉዳይ ዋናው የኦዲት ትኩረት መስክ እንዲሆን በማድረግ የቁጥጥር ሥርዓቱ መጠናከር አለበት፡፡

## አንቀጽ 11
## ስለተሻሩ መመሪያዎች

1. በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ሰኔ 29/2004 ዓ.ም በቁጥር ሲ.ሰ.ሚ30/ጠ13/40/883 በተጻፈ ደብዳቤ ተላልፎ በሥራ ላይ ያለው የመንግሥት ሠራተኞች ቀን ውሎ አበል ክፍያ አፈጻጸም በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

2. ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ሌሎች የመንግሥት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል አከፋፈል ሰርኩላሮችና ልማዳዊ አሠራሮች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

## አንቀጽ 12
## በዚህ መመሪያ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች

በዚህ መመሪያ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ጥያቄው ለኮሚሽኑ እየቀረበ ውሳኔ የሚሰጥባቸው ይሆናል።

## አንቀጽ 13
## መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከየካቲት 16 ቀን 2012 ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

በዛብህ ገብረየስ
የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን
ኮሚሽነር

## ሠንጠረዥ አንድ

## የክልል ዋና ከተሞችና የሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች የቀን ውሎ አበል መጠን

| ተ.ቁ | የክልሉ ዋና ከተማ ወይም የከተማ አስተዳደሩ ስም | የደመወዝ መጠንን መሰረት ያደረገ የአበል መጠን | | |
|---|---|---|---|---|
| | | እስከ ብር 3,933 | ከብር 3,934 እስከ ብር 9,055 | ብር 9,056 እና በላይ |
| 1 | መቀሌ | 348 | 395 | 468 |
| 2 | ሰመራ | 315 | 361 | 413 |
| 3 | ባህርዳር | 344 | 390 | 462 |
| 4 | አሶሳ | 328 | 367 | 416 |
| 5 | ጅግጅጋ | 314 | 353 | 404 |
| 6 | ጋምቤላ | 327 | 367 | 419 |
| 7 | ሀረር | 365 | 407 | 465 |
| 8 | ሀዋሳ | 359 | 405 | 477 |
| 9 | አዲስ አበባ | 468 | 549 | 724 |
| 10 | ድሬዳዋ | 367 | 408 | 465 |

## ሠንጠረዥ ሁለት

## የአዳማ ከተማ አስተዳደር የቀን ውሎ አበል መጠን

| ተ.ቁ | የከተማ አስተዳደሩ ስም | የደመወዝ መጠንን መሰረት ያደረገ የአበል መጠን | | |
|---|---|---|---|---|
| | | እስከ ብር 3,933 | ከብር 3,934 እስከ ብር 9,055 | ብር 9,056 እና በላይ |
| 1 | አዳማ ከተማ አስተዳደር | 353 | 396 | 459 |

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Civil Service Commission

## ሠንጠረዥ ሶስት

## በየክልሉ ስር ያሉ የዞን ዋና ከተሞች የቀን ውሎ አበል መጠን

| ተ.ቁ | ክልሎች | የደመወዝ መጠንን መሰረት ያደረገ የአበል መጠን | | |
|---|---|---|---|---|
| | | እስከ ብር 3,933 | ከብር 3,934 እስከ ብር 9,055 | ከብር 9,056 እና በላይ |
| 1 | የትግራይ ብ/ክ/መንግሥት | 279 | 330 | 417 |
| 2 | የአፋር ብ/ክ/መንግሥት | 283 | 322 | 385 |
| 3 | የአማራ ብ/ክ/መንግሥት | 277 | 327 | 409 |
| 4 | የኦሮሚያ ብ/ክ/መንግሥት | 308 | 348 | 402 |
| 5 | የቤንሻ/ጉሙዝ ክ/መንግሥት | 270 | 311 | 366 |
| 6 | የደቡ/ብ/ብ/ህ ብ/ክ/መንግሥት | 283 | 325 | 383 |
| 7 | የጋምቤላ ብ/ክ/መንግሥት | 279 | 323 | 387 |
| 8 | የሱማሌ ብ/ክ/መንግሥት | 262 | 308 | 378 |

## ሠንጠረዥ አራት

## በየክልሉ ስር ያሉ የወረዳ ዋና ከተሞች ወይም ከተማ አስተዳደሮች

## የቀን ውሎ አበል መጠን

| ተ.ቁ | የክልሎች ስም | የደመወዝ መጠንን መሰረት ያደረገ የአበል መጠን | | |
|---|---|---|---|---|
| | | እስከ ብር 3,933 | ከብር 3,934 እስከ ብር 9,055 | ብር 9,056 እና በላይ |
| 1 | የትግራይ ብ/ክ/መንግሥት | 267 | 336 | 357 |
| 2 | የአፋር ብ/ክ/መንግሥት | 251 | 293 | 353 |
| 3 | የአማራ ብ/ክ/መንግሥት | 254 | 292 | 340 |
| 4 | የኦሮሚያ ብ/ክ/መንግሥት | 259 | 301 | 363 |
| 5 | የቤን/ጉምዝ ብ/ክ/መንግሥት | 231 | 266 | 303 |
| 6 | የደቡ/ብ/ብ/ህ ክ/መንግሥት | 249 | 288 | 339 |
| 7 | የጋምቤላ ብ/ክ/መንግሥት | 234 | 274 | 328 |
| 8 | የሱማሌ ብ/ክ/መንግሥት | 237 | 275 | 323 |

**የመንግሥት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል ክፍያ መጠየቂያና መፍቀጃ**

**አባሪ**

| ተ.ቁ | የቀን ውሎ አበል መጠየቂያና መፍቀጃ | | የክፍያ ዓይነት | የክፍያ መጠን |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የተቋም ስም | | በቅድሚያ የተከፈለ | |
| 2. | ፕሮግራም/ የሥራ ሂደት | | ለውሎ አበል ብር | |
| 3. | የፕሮጀክት ስምና ኮድ | | ለአየር ፀባይ አበል | |
| 4 | የጉዞው ዓላማ/ ምክንያት | | ለነዳጅ/ቅባት ብር | |
| 5 | የጉዞው መነሻ | | ለመጠባበቂያ ብር | |
| 6 | የጉዞው መድረሻ | | በጠቅላላ የተከፈለ | |

የሠራተኛው ስም..................

ፊርማ................

የሥራ ኃላፊ

ስም.........................

ፊርማ.....................

ሂሳቡን ያረጋገጠው ስም.............

ፊርማ.............

የተቋሙ ማህተም

ግልባጭ

- ለፋይናንስና ግዥ ዳይሬክቶሬት

## የመንግሥት ሠራተኞች ውሎ አበል ክፍያ ማወራረጃ ቅጽ

1. የመሥሪያ ቤቱ ስም.................................
2. ፕሮግራም/የሥራ ሂደት............................
3. የሠራተኛው ስም....................................
4. ደመወዝ መጠን......................................
5. የመጓጓዣ ዓይነት...................................
6. የውሎ አበል አከፋፈል ስሌት ሠንጠረዥ

ሀ/ ሠራተኛው በጉዞ ላይ የቆየበት ቦታዎች (ለቁርስ ፣ ለምሳ፣ ለዕራት) መግለጫ ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | መነሻ | | | የደረሰበት ቦታ | | | | በፋይናንስ ባለሙያ ብቻ የሚሞላ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቦታ | ቀን | ሠዓት | ቀን | ቁርስ | ምሳ | እራት | የቀን ብዛት | የውሎ አበል መጠን | የአየር ፀባይ አበል | ድምር |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | ድምር | | | |

ለ/ ሠራተኛው ለሥራ በቆየባቸው ቦታዎች መግለጫ ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | ቀን | ለሥራ የታደረበት ቦታ ክልል/ ዞን /ወረዳ/ ከተማ | የቀን ብዛት | በፋይናንስ ባለሙያ ብቻ የሚሞላ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የውሎ አበል | የበረሃ አበል | ድምር |
| | | | | | | |
| | | | | | | |

ሐ/ አጠቃላይ የውሎ አበልና ነዳጅ ክፍያ ማጠቃለያ ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | የክፍያ ዓይነት | ቅድሚያ የተከፈለ የገንዘብ መጠን | ተጨማሪ ክፍያ | ተመላሽ የሚደረግ ገንዘብ መጠን | ድምር/ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የውሎ አበል | | | | |
| 2 | የነዳጅ | | | | |
| 3 | የጥገና | | | | |
| 4 | ሌላ | | | | |
| | ጠቅላላ ወጪ | | | | |

የሠራተኛው ሰም................ ሂሳቡን ያዘጋጀው ሠራተኛ

ፊርማ........... ፊርማ .....................

ያረጋገጠው ኃላፊ ስም.......... ሂሳቡን ያረጋገጠው ኃላፊ ስም------

ፊርማ................... ፊርማ -------------------------